Australian
Human Rights
Commission
*everyone, everywhere, everyday*

# ቅሬታ/ስሞታ ስለማቅረብ

የአውስትራሊያ ሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ኮሚሽን ያለምንም ተጽእኖ በራሱ የሚተዳደር አካል እንደሆነና ህገወጥ በሆኑ የጾታ፤ በዘር ጎሳ፤ አካለ ጉዳተኛ መሆን እና በእድሜ አድልዎ ፈጠራ፤ በILO III አድልዎ ፈጠራና ሰብአዊ መብቶችን በመጣስ ለሚቀርቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ መፍትሄ ይሰጣል።

## ለእኛ ምን ዓይነት ቅሬታ ማስገባት እንደሚችሉ

- ***በጾታ አድልዎ ፈጠራ*** ላይ የሚካተት በወሲባዊ፤ የጾታ መለያ፤ የጾታ ለውጥ፤ እርግዝና፤ የጋብቻ ወይም ግንኙነት ሁኔታ፤ ጡት የማጥባት፤ በቤተሰብ ሃላፊነቶችና በወሲባዊ አፈጻጸም ጋር በተዛመደ አስመልክቶ ለሚፈጠር ወሲባዊ ማስፈራራት ወይም አድልዎ ፈጠራ ይሆናል።
- ***በአካለ ጉዳተኛ በመሆን አድልዎ ፈጠራ*** ላይ የሚካተት በአካላዊ፤ እውቀት፤ ስሜታዊ፤ በመማርና ስነ- ኣእምሮ ጉዳተኛ መሆን፤ በሽታ ወይም ህመም፡ በጤና ሁኔታ፡ ከሥራ ጋር በተዛመደ ጉዳት፤ ባለፈ፤ አሁንና ለወደፊት የሚኖር አካለጉዳተኛ መሆን እንዲሁም የአካለ ጉዳተኛ እርዳታ ማግኘት፤ ከእንስሳት ጋር በተዛመደ እርዳታ አቅራቢ አካለጉዳተኛ ሰው ላይ አድልዎ ፈጠራን ያካትታል።
- ***በዘር ጎሳ አድልዎ ፈጠራ*** ላይ የሚካተት በዘር ጎሳ፤ በቆዳ ቀለም፤ በትውልድ ዘር፤ በመጣበት አገር ወይም ጎሳ እና የስደተኛ ሁኔታን አስመልክቶ ጥላቻንና አድልዎ ፈጠራን ይሆናል።
- ***በእድሜ አድልዎ ፈጠራ*** ላይ የሚካተት በጣም ወጣት ወይም የእድሜ ሽማግሌ መሆን አስመልክቶ አድልዎ ፈጠራን ይሆናል።
- ***በ ILO III አድልዎ ፈጠራ*** ላይ የሚካተት በሥራና ሰራተኛ፤ በሃይማኖት፤ በወንጀል ሪኮርድ፤ በንግድ ማሕበር እንቅስቃሴ፤ በፖለቲካ አመለካከትና በመጣበት ማሕበራዊ ሁኔታ አስመልክቶ አድልዎ ፈጠራን ይሆናል።
- ***በሰብአዊ መብቶች*** ላይ የሚካተት በኮመንወልዝ መንግሥት ወይም በመወከል ለሚደረግ ድርጊት ይህም ለአንዳንድ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አሰራሮች፤ እንደ በሲቪልና በፖለቲካዊ መብቶች ላይ የዓለም አቀፍ ስብሰባ፤ በህጻን መብቶች ላይ ስምምነት እና አካለጉዳተኛ በሆነ ሰው መብቶች ስምምነት በመጣስ ለሚቀርብ ክስ ያካትታል።

አውስትራሊያ በየትኛውም ቦታ ሆኖ ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችሉና ለማመልከት ምንም አያስከፍልም። በቅሬታ አሰራር ሂደት ያሉት ደረጃዎች ከዚህ በታች ተገልጿል።

## ጥያቄ ማቅረብ

- እርግጠኛ ካልሆኑ፤ ስለሆነ ነገር ቅሬታ ማድረግ ከፈለጉ፤ የኮሚሽን አገር አቀፍ መረጃ አገልግሎትን በስልክ **1300 656 419** ደውሎ ማነጋገር ወይም በኢሜል infoservice@humanrights.gov.au አድርጎ ማነጋገር
- የሥራ ሂደቱን ለመጀመር የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጹን ለርስዎ መላክ እንችላለን።
- ልንረዳዎት ካልቻልን፤ ሊረዳዎ ወደሚችል የሆነ ሰው ስምዎን ለማስተላለፍ እንሞክራለን።

## ቅሬታ ማቅረብ

- ቅሬታው በጽሁፍ መሆን አለበት። ለቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ሞልተው በፖስታ ወይም በፋክስ አድርጎ ወደ እኛ መላክ ይችላሉ ወይም በመስመር ላይ በእኛ ድረገጽ፡ www.humanrights.gov.au አድርጎ ማስገባት ይቻላል።

April 2020

- በሚፈልጉት ቋንቋ አድርጎ ቅሬታዎን ማስገባት እንደሚችሉና አስፈላጊ ከሆነም ያለዎትን ቅሬታ ለመጻፍ መርዳት እንችላለን።
- ቅሬታ ለማስገባት የህግ ጠበቃ አያስፈልግዎትም።
- ካለዎት ቅሬታ ጋር መደራደር ካልቻልን ለምን እንደሆነ እንገልጻለን።

## ማጣራት

- ስለርስዎ ቅሬታ ለማነጋገር እንደምንገናኝና ታዲያ የበለጠ መረጃ እንዲሰጡን ልንጠይቅዎ እንችላለን።
- በአጠቃላይ ስላቀረቡት ቅሬታ ኮሚሽኑ ለግለሰቡ ወይም ቅሬታ ላቀረቡበት ድርጅት በማነጋገር የርስዎን ቅሬታ ቅጂውን ለመስጠት ይሆናል። ለየት ያለ መረጃ እንዲያቀርቡ ልንጠይቃቸው እንደምንችል እና/ወይም የርስዎን ምላሽ እናቀርባለን። የርስዎን ቅሬታ በተመለከተ ለኮሚሽኑ በተሰጠ መረጃ ላይ ግላዊነት የያዘ ማለት ስለርስዎ ስሜታዊ የሆነ መረጃን ሊያካትት ይችላል።
- በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከርስዎ ቅሬታ ጋር መደራደሩን ላለመቀጠል መወሰን እንችል ይሆናል፤ ለዚህም ምክንያቱን እንገልጻለን።
- ቅሬታውን በእርቅ ድርድር መፍትሄ ለማግኘት ስለመሞከር ልናነጋግርዎ እንችል ይሆናል።

## እርቅ/መማከርት

- መማከርት ማለት እርስዎን ወይም ቅሬታ ለቀረበለት ድርጅት ተወካይ ሰው በማነጋገር ስለ ጉዳዩ መፍትሄ ማስገኛ መንገድ በመፈለግ ለመርዳት እንሞክራለን።
- መማከርቱ ‘የማስታረቂያ ስብሰባ’ ተብሎ በሚጠራ በአካል ቀርቡ ስብሰባ ወይም በተለፎን ተደርጎ ስብሰባ ሊካሄድ እንደሚችል ነው። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ በኢሜል አድርጎ ከአማካሪው ጋር በመነጋገር ቅሬታው መፍትሄ ማግኘት ይችላል።
- ቅሬታዎች በተለያዩ ብዙ መንገዶች መፍትሄ ማግኘት ይችላሉ። ለምሳሌ፡ ይቅርታ በመጠየቅ፤ ፖሊሲን በመቀየር ወይም የካሳ ክፍያ በማድረግ።

## ለፍርድ ቤት እርምጃ ሊወሰድ የሚችል – ወሲብ፤ አካለጉዳተኛ፤ ዘር ጎሳ እና በእድሜ አድልዎ ፈጠራ

- በህገወጥ አድልዎ ፈጠራ ከተፈጸመ ኮሚሽኑ ለመወሰን ሥልጣን የለውም።
- የርስዎ ቅሬታ መፍትሄ ካላገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ከተቋረጠ ታዲያ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ መቻል ይኖርብዎታል። ህገወጥ የሆነ አድልዎ ፈጠራ ተፈጽሞ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ነው መወሰን የሚችል።
- ወደ አውስትራሊያ ፈደራል ሰርኩት ፍርድ ቤት ወይም የአውስትራሊያ ፈደራል ፍርድ ቤት ማመልከቻ ለማስገባት ቅሬታዎ በኮሚሽኑ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ 60 ቀናት ይኖርዎታል።
- ኮሚሽኑ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ወይም በፍርድ ችሎት የርስዎን ጉዳዩ ለመርዳት መወከል አይችልም።
- ጉዳይዎን ወደ ፍርድ ቤት የሚወስዱት ከሆነ ከህግ ጠበቃ ወይም ህጋዊ የሆነ አገልግሎት ማነጋገር ሊያስፈልግዎት ይችላል።

## ውሳኔ/ሪፖርት – የILO III አድልዎ ፈጠራና ሰብአዊ መብቶች

- ቅሬታው መፍትሄ ካላገኘ ወይም በአንዳንድ ሌላ ምክንያት ካቋረጠ፣ ለ ILO III አድልዎ ፈጠራ ወይም ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ስለመፈጸሙ የኮሚሽኑ ፕሬዚደንት ሊወስኑ ይችላሉ።

- ለአድልዎ ፈጠራ ወይም ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት መፈጸም ፕረሲደንቱ ካመኑበት ወደ ፌደራል አቃቤህግ-ጠቅላይ ፍርድ ቤት/ Federal Attorney-General ሪፖርት ማድረግ ይችል ይሆናል። በሪፖርቱ ውስጥ ፕረዚደንቱ መምከር የሚችሉት ግለሰቡ ላጣው የሆነ ነገር ወይ ለደረሰበት ጉዳት የገንዘብ ካሳ ግምት ውስጥ ማስገባት። ሪፖርቱ በፓርላመንቲ ጠረጴዛ ላይ ሊቀርብ ይችላል።

- ስለ አድልዎ ፈጠራና ሰብአዊ መብቶች ጥሰት ፕረሲደንቱ የሰጡት ምሳሌዎችን በኮሚሽኑ ድረገጽ፡ http://www.humanrights.gov.au/publications/reports-minister-under-ahrc-act ላይ ማየት።

## በበለጠ መረጃ የት ማግኘት እችላለሁ?

ለአውስትራሊያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ለማነጋገር ዝርዝር መረጃዎች:

**ተለፎን**
የአገር አቀፍ መረጃ አገልግሎት በስልክ: 1300 656 419
መስማት ለተሳነው/TTY: 1800 620 241
NRS 133 677
ፋክስ: (02) 9284 9611

አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎት ከሆነ በስልክ **131 450** አድርጎ መደወልና ወደ አውስትራሊያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እንዲያነጋግርዎት መጠየቅ።

ደንቆሮ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት ለTTY በስልክ 1800 620 241 አድርጎ እኛን ማነጋገር ይችላሉ። ደንቆሮ ወይም የመስማት ወይም የመናገር ችግር ካለብዎት በአገራዊ የቅብብሎሽ አገልግሎት (NRS) በስልክ 133 677 አድርጎ ማነጋገር ይችላሉ። በምልክት/Auslan አስተርጓሚ ካስፈለግዎት ልናቀናጅልዎ እንችላለን።

አይነ ስውር ወይም የማየት ችግር ካለብዎት መረጃን በሌላ ቅርጽ ዚጠይቁ ማቅረብ እንችላለን።

**በፖስታ**

GPO Box 5218
Sydney NSW 2001

**በመስመር ላይ**
ኢሜል: infoservice@humanrights.gov.au
ድረገጽ: www.humanrights.gov.au

በመስመር ላይ ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉት በድረገጽ፡
http://www.humanrights.gov.au/complaints/lodging-your-complaint ላይ በመግባት ነው።

## አጠቃላይ ህጋዊ የሆነ ምክር

ቅሬታ ለማቅረብ እያሰቡ ከሆነ፣ ህጋዊ የሆነ ምክር ማግኘት ሊያስፈልግዎት ይችላል። ስለ አድልዎ ፈጠራና ማስፈራራት በተመለከተ ህጋዊ የሆነ ምክር ያለክፍያ በነጻ ማቅረብ የሚችሉ የማህበረሰብ ህጋዊ ምክር አገልግሎቶች እንዳሉ ነው።

ለህጋዊ የሆነ እርዳታ አካል ማነጋገር የሚችሉት በድረገጽ፡ (https://www.nationallegalaid.org/for-individuals/) ወይም በአቅራቢያዎ ለሚገኝ የማህበረሰብ ህጋዊ ምክር አገልግሎት በድረገጽ፡ (www.naclc.org.au/directory) ይሆናል።

**የክህደት ቃል: በዚህ እውነታ ጽሁፍ ላይ ያለው መረጃ እንደ መመሪያ ብቻ ተብሎ የታሰበ ነው። ለህጋዊ የሆነ ምክርን እንደማተካ ነው።**